አፍሪካ ቲቪ

5

# አፍሪካ አካዳሚ
AFRICA ACADEMY

ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት

# የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

# ሱረቱ አል-ካፊሩን

- (የከሓዲያን ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው:: የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (6) ናቸው::

## ከምዕራፉ ዓላማዎች፦

- የአላህን ብቸኛ ተመላኪነትን እና ከእርሱ ጋር ተጋሪ ከማድረግ መታቀብን በማፅደቅ እንዲሁም በእስልምናና በአጋሪነት መካከል ሙሉ በሙሉ ፍፁም መገናኘት የማይቻልበት ልዩነት መኖሩን የሚያረጋግጥ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- ከከሓዲያን ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-የተወሰኑ አልአስወድ ብኑ አብዱል ሙጠሊብ፤ ወሊድ ኢብኑ ሙጊራህ፤ ኡመየት ኢብኑ ኸለፍ አልዓሲ ከነብዩ (صلى الله عليه وسلم (ጋር በጠዋፍ ላይ ተገናኝተው ገንዘብ ከፈለክ የፈለከውን ያህል እንስጥህ ሴት ከፈለክ የፈላካት ምረጥና እንዳርልህ ስልጣን ከፈለክ እናንግስህ ብቻ አምላካችንን ተውልን እንስማማ በዚህ ካልተስማማህ ደግሞ አንድ ዓመት ያንተን ጌታ በሌላው ዓመት ደግሞ የእኛን ጌታ አብረን እንገዛ በማለት ለድርድር ሲቀርቡ ነብዩ (صلى الله عليه وسلم (ጌታዬ የሚለኝን እጠብቃለሁ በማለታቸው ነው፡፡ (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)
- በሌላ ሐዲስም ሌላ ዘገባ መጥተዋል፡፡



www.AfricaAcademy.com
AAcademyEthio

- (1) (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ለካሓዲያን)፡- <<እናንተ በአላህ የካዳችሁ ከሀዲያን ሆይ!>> በላቸው፡፡
- (2) ‹‹አሁንም ሆነ ወደፊትም እናንተ የምታመልኩትን ጣዖት አላመልክም፡፡
- (3) እኔ የማመልከውን አላህን እናንተ የምታመልኩ አይደላችሁም፡፡
- (4) እናንተ የምታመልኩትን ጣዖትም እኔ የማመልክ አይደለሁም፡፡
- (5) እኔ የማመልከውን አላህን እናንተ የምታመልኩ አይደላችሁም፡፡
- (6) ለራሳችሁ የፈጠራችሁት ሃይማኖት አላችሁ፤ ለኔ አላህ ያወረደልኝ ሃይማኖቴ አለኝ፡፡››

5

- **ከከሐዲያን ምዕራፍ ከአንቀፅ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**
- 1. እምነት ማለት፡- በጣኦት ያለመነ፤ ከሃዲ ማለት በጣኦት አምኖ በአላህ የካደ መሆኑን፤
- 2. አላህ ነብዩ صلى الله عليه وسلم የከሐዲያንን አስተሳሰብ እንዳቀበሉ የወሰደው ኃላፊነት፤
- 3. በኩፍር ሰዎችና በእምነት ሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባው በእምነት ጉዳይ ላይ ለምንም ተብሎ መደራደር እንደማይቻል፤
- 4. በእውነቱ ላይ መድረስ ካልተቻለ ሁሉም የየራሱን ይዞ ለጊዜው መቀጠል ለአፍታም ቢሆን ከኩፍር ጋር መደራደር እንደማይቻል እንማራለን፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com